መልእክት ሁለት

## የሕይወት መስመር በኖኅ ዘንድ—<br>ዘመኑን የሚቀይር ኑሮና ሥራ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ዘፍ. 6፥5-14፤ ዕብ. 11፥7

**I. ኖኅ በእግዚአብሔር አመነ፣ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ፣ እግዚአብሔርን ደስ አሰኘ፣ እግዚአብሔር የሆነውንም ሁሉ ተደሰተ፦**

ሀ. ሰይጣን ሰውን ፍጽሞ አበላሽቶ ነበር፤ እግዚአብሔርም ለዓላማው የፈጠረውን ሰው ለማጥፋት ቆርጦ ነበር።

ለ. ከዚህም የተነሣ፣ እግዚአብሔር የተሸነፈ ይመስል ነበር፤ *ኖኅ ግን* የሚለው እግዚአብሔር ከሰው ጋር የነበረውን የመጀመሪያውን ዓላማ ማከናወኑን ይቀጥል ዘንድ ለእግዚአብሔር መንገድ የሰጠውን ሉዓላዊ መንስኤ ይጠቁማል።

ሐ. በኖኅ ሕይወትና ሥራ በኩል፣ እግዚአብሔር በጠላቱ ላይ ድልን ተቀዳጀ፤ ዘመኑንም ቀየረ።

**II. የኖኅ ኑሮ ዘመኑን የቀየረ ኑሮ ነበር—ተዛ. ፊልጵ. 1፥19-21፦**

ሀ. ዘመኑን የሚቀይር ኑሮ የቀደሙ አባቶችን እግዚአብሔርን የመምሰል መንገዶች የሚወርስ ኑሮ ነው፦

1. ኖኅ ክርስቶስ የሴቲቱ ዘር የመሆኑን የተስፋ ቃል እና እግዚአብሔርን እንደሚያረካው ጽድቅ የክርስቶስን መሸፈን በመቀበል የአዳምን የመዳን መንገድ ወርሷል—ዘፍ. 3፥15፣ 20-21፤ ተዛ. ኢሳ. 12፥2።
2. ኖኅ ክርስቶስን ለኃጢአቶቻችን እንደሆነ መሥዋዕት ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን ለማስደሰት እንደሆነ ስጦታ ለእግዚአብሔር የማቅረብን የአቤልን የመሠዋት መንገድ ወርሷል—ዘፍ. 4፥4።
3. ኖኅ [ያሕዌ] የሆነውን ሁሉ ለመደሰት የያሕዌን ስም የመጥራትን የሄኖስን መንገድ ወርሷል—ቁ. 26፤ ኤር. 33፥3፤ ሮሜ 10፥12፤ 2 ጢሞ. 2፥22።
4. ኖኅ እግዚአብሔርን እንደ ማዕከላችን እና እንደ ሁሉ ነገራችን መውሰድን፣ በእግዚአብሔር መሠረትና ከእግዚአብሔር ጋር መኖርና ሁሉንም ነገሮች ማድረግ የሆነውን አካሄድን ከእግዚአብሔር ጋር የማድረግን የሄኖክን አካሄድ ወርሷል—ዘፍ. 5፥22-24፤ ዕብ. 11፥5-6፤ 2 ቆሮ. 5፥4፣ 9፣ 14-16፤ 6፥1።

ለ. ኖኅ እየኖረበት የነበረውን የተበላሸ ዘመን እውነተኛ ሁኔታ እግዚአብሔር አሳየው —ዘፍ. 6፥3፣ 5፣ 11፣ 13፤ ማቴ. 24፥37-39፤ 2 ጢሞ. 3፥1-5።

ሐ. "ኖኅ *ግን* በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን [ጸጋን] አገኘ"—ዘፍ. 6፥8፦

1. ሰይጣን ሁኔታውን ለማበላሸት የተቻለውን ሁሉ ባደረገበት ጊዜ፣ ሁልጊዜም ዘመኑን የቀየሩ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋን ያገኙ ሰዎች ነበሩ—ተዛ. ዳን. 1፥8፤ 9፥23፤ 10፥11፣ 19።
2. የዘፍጥረት ዘገባ ዋና ዓላማ ውድቀትን ለማሳየት ሳይሆን የእግዚአብሔር ጸጋ ለወደቁ ሰዎች ምን ያህል ማድረግ እንደሚችል ለማሳየት ነው፦
   ሀ. ጸጋ ሁሉን ነገር ይሆንልን ዘንድ እና ሁሉን ነገር በእኛ ውስጥ፣ በእኛ በኩልና ለእኛ ያደርግ ዘንድ የተደሰትነው የእግዚአብሔር መገኘት ፣ እግዚአብሔር ራሱ ነው—ዮሐ. 1፥14፣ 16-17፤ ራእ. 22፥21።
   ለ. ጌታን እንደ ጸጋ መደሰት ያለው እርሱን ከሚወዱት ጋር ነው—ኤፌ. 6፥24፤ ዮሐ. 21፥15-17።
   ሐ. የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ጸጋ እንደ የሦስታንዱ አምላክ የተትረፈረፈ አቅርቦት የምንደሰተው የስብዕና መንፈሳችንን በማንቀሳቀስ ነው—ዕብ. 10፥29፤ ገላ. 6፥18፤ ፊልጵ. 4፥23፤ ፊልሞ. 25፤ 2 ጢሞ. 4፥22።
   መ. የእግዚአብሔር ቃል የጸጋ ቃል ነው—ሐዋ. 20፥32፤ ቆላ. 3፥16፤ ተዛ. ኤር. 15፥16።
   ሠ. በሂደት ያለፈውን ሦስታንዱን አምላክ እንደ የሕይወት ጸጋ የምንለማመደው በአንድነት መቆሚያ ስፍራ ላይ ከቅዱሳን ጋር በመሰብሰብ ነው—መዝ. 133፥3፤ 1 ጴጥ. 3፥7፤ ሐዋ. 4፥33፤ 11፥23።
   ረ. ጌታን እንደሚጨምር እና ለሁሉ እንደሚበቃ ጸጋችን በመከራዎችና በፈተናዎች ውስጥ መለማመድ እንችላለን—2 ቆሮ. 12፥9።
   ሰ. በጸጋው ኃይል ለጌታ መድከም ያስፈልገናል—1 ቆሮ. 15፥10፣ 58፤ 3፥12።
   ሸ. የእግዚአብሔር ልዩ ልዩ ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች መሆን ያስፈልገናል—1 ጴጥ. 4፥10፤ ኤፌ. 3፥2፤ 2 ቆሮ. 1፥15፤ ኤፌ. 4፥29።

ቀ. በጸጋ ኃይል፣ በጸጋ ብርታት እና በጸጋ ሕይወት፣ ከእግዚአብሔር ጋርና አንዳችን ከሌላችን ጋር ትክክል መሆን እንችላለን፤ ጸጋ ጽድቅን ያፈራል—ዕብ. 11፥7፤ ሮሜ 5፥17፣ 21።

**III. የኖኅ ሥራ ዘመኑን የቀየረ ሥራ ነበር—1 ቆሮ. 3፥9፤ 2 ቆሮ. 6፥1፤ ማቴ. 16፥18፤ 1 ቆሮ. 3፥12፦**

ሀ. እግዚአብሔር ለኖኅ ሁሉን ያካተተ መገለጥ፣ ተጨማሪ መገለጥ፣ እግዚአብሔር የተበላሸውን ትውልድ የሚያስወግድበትን እና አዲስን ዘመን የሚያመጣበት መንገድ የነበረውን መርከቡን የመገንባት መገለጥ ሰጠው፦

1. መርከቡ የክርስቶስ ምሳሌ ነው (1 ጴጥ. 3፥20-21)—የክርስቶስ ብቻ ሳይሆን በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም የሚጠናቀቀው የክርስቶስ አካል እና አዲሱ ሰው የሆነው ከብዙዎች የሆነው ክርስቶስ፣ የቤተ ክርስቲያንም [ምሳሌ] ነው (ማቴ. 16፥18፤ 1 ቆሮ. 12፥12፤ ኤፌ. 2፥15-16፤ ቆላ. 3፥10-11፤ ራእ. 21፥2)።
2. የመርከቡ መገንባት፣ እንደ ግንባታ ዕቃ በክርስቶስ ብልጥግናዎች ንጥረ-ነገር ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ በሚሠሩት የሚገነባውን ከብዙዎች የሆነውን ክርስቶስ በምሳሌ ያሳያል—1 ቆሮ. 3፥9-12፤ ኤፌ. 4፥12፤ 2፥22።
3. ይህ ግንባታ የእግዚአብሔር በሥጋ መገለጥ ይሆኑ ዘንድ ሰዎችን በክርስቶስ አንድ ላይ ለመገንባት ክርስቶስ ወደ እነርሱ ውስጥ መሠራቱ ነው—1 ጢሞ. 3:15-16፦
   - ሀ. በሥራችን ውስጥ ወሳኙ ጉዳይ ሦስታንዱ አምላክ ራሱን ወደ ማንነታቸው ውስጥ ይገነባ ዘንድ የሚገነባውንና የተገነባውን አምላክ ወደ ሌሎች ውስጥ ማገልገል ነው—ማቴ. 16፥18፤ ኤፌ. 2፥21-22፤ 3፥17፤ 1 ቆሮ. 14፥4።
   - ለ. አንድን ነገር በተግባር መለማመድ ያስፈልገናል—ራሱን ወደ ውስጡ ሰዋቸው ውስጥ ይገነባ ዘንድ በሂደት ያለፈውንና የተጠናቀቀውን ሦስታንዱን አምላክ ወደ ሌሎች ውስጥ ማገልገል፤ ጌታ በዚህ መንገድ እንሠራ ዘንድ እንዲያስተምረን መጸለይ ያስፈልገናል—2 ቆሮ. 13፥14፤ 1 ቆሮ. 3፥9፣ 10፣ 12፤ ሮሜ 11፥36።

ለ. ቤተ ክርስቲያንን በመገንባትና ወደ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ በመግባት፣ በታላቁ መከራ በዛሬው ክፉ ትውልድ ላይ ከሚሆነው ከእግዚአብሔር ፍርድ እንድናለን፣ ወደ አዲስ ዘመን፣ ወደ ሺው ዓመት ዘመን ለመግባትም ከዚያ ትውልድ እንለያለን—ዕብ. 11፥7፤ ማቴ. 24፥37-39፤ ሉቃ. 17፥26-27።

© 2026 Living Stream Ministry